# የያዕቆብ መልዕክት (40)

## <u>ጥናት አንድ ያዕ 1፡1-12</u>

የጥናት ዓላማ፡- እንደ ጌታ ደቀመዝሙር፤ መከራ ሲደርስብን፣ ሲያጠን ወይም ተስፋ ሲያስቆርጠን የመጣ ሳይሆን፤ በአንጻሩ በህይወታችን ትዕግስትን በማፍራት ወደ ፍጹምነት ልናድግ የሚያስችለን መሰላል አድርገን ልንመለከተው እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ወንድሞቼ ሆይ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት፤ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ፡፡›› ያዕ 1፡2-3

1. ያዕ 1፡1-12 በአንድነት ይነበብ፡፡ ስለመልዕክቱ ጸሐፊና ስለተጻፈላቸው ሰዎች ከምንባቡ ውስጥ የምትመለከተውን ተናገር፡፡ ያዕቆብ በመልዕክቱ መጀመሪያ ራሱን በምን ዓይነት ነው የሚያስተዋውቀው?
2. ዳንኤል2፡21፣ መዝሙር 111፡10፣ ምሳሌ 13፡20ንና መክብብ 7፡25ትን በማንበብ የሰው ልጅ ዕውቀትን ለማግኘት የሚችልባቸውን መንገዶች ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል በቁ5 ላይ ጥበብ ስለሚገኝበት መንገድ በተለይ በዳን 2፡21 ከተነገረው ጋራ የሚለይበትን መንገድ አስረዳ፡፡
3. ቁ5ትን በእርጋታ በማንበብ፤ እግዚአብሄር ጥበብን ስለሚሰጥበት መንገድ የተነገሩ አራት ነገሮችን ነገሮች ምን ምንድናቸው? ጥበብ እንደጎደለህ ስታውቅ በመጀመሪያ የምትሄደው ወደማን ነው?
4. ከሰጪው አንጻር ይህንን የሚመስል ከሆነ ከተቀባዩ ስለሚጠበቀው ነገርስ ያዕቆብ የሚነግረን አንድ ዋነኛ ነገር ምንድነው? ተጠራጣሪን ሰው ከምን ጋራ ነው ጸሐፊው የሚያነጻጽረው? ያዕቆብ በዚህ ክፍል በሚናገረው ባለማመንህ ምክንያት ከእግዚአብሄር ያልተቀበልከው ነገር አለወይ? ከዚህ አንጻር ምን መለወጥ ታስባለህ?
5. በቁ9 ላይ ዝቅ ያለው በከፍታው፣ ባለጸጋውም በውርደቱ እንዲመካ የሚለውን ምክር የሰጠበት ዋነኛ የምትለው ምክንያት ምንድነው?
6. ቁ2-3 ላይተመልሰን ስናነብ ያዕቆብ ለአንባቢዎቹ መከራን አስመልክቶ የሚሰጠው ምክር ምን የሚል ነው? ሊገጥሟቸው ስለሚችሏቸው የመከራ አይነቶችስ ጸሃፊው ምን ይነግራቸዋል? በነዚህ የመከራ ዓይነቶች ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ የምትሏቸውን ጥቂቶቹን በመዘርዘር ተወያዩባቸው፡፡
7. ይህ ‹‹እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት›› የሚለው አነጋገር የመከራው ክብደት አይሰማችሁ፣ በአዕምሯችሁ አቅልላችሁ ተመልከቱት ወይም ደግሞ በሳቅና በፈገግታ አሳልፉት ማለቱ ነው ወይ? ይህንን ማለት ካልሆነስ ያዕቆብ ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
8. ይህ መከራን በሙሉ ደስታ መቀበል የሚለው አመለካከት ማንኛውንም ሰው የሚያጠቃልል ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ያዕቆብ መከራን አስመልክቶ ያውቃሉ በማለት የገመተው አንድ ነገር ምንድነው? የዚህ እውቀትና በመከራ የመደሰት ህይወትን ተለማምደሃል ወይ? መከራ ሲሰብርህና ተስፋ ሊያስቆርጥህ የሚመጣ ነገር ሳይሆን ትዕግስትን ሊያስገኝና ወደ ፍጹምነት ልታድግ የምትችልበት መሰላል አድርገህ ማየትን ተለማመድ፡፡

# ጥናት ሁለት ያዕ 1፡13-27

የጥናት ዓላማ፡- ሃይማኖታችን በእግዚአብሄር ፊት ተቀባይነት የሚኖረው በሁለት አቅጣጫ ስናድግና ስንሰፋ ነው፤ ይኸውም አንደኛው ሌሎችን በችግራቸው መርዳት የሚገባን ሲሆን ሁለተኛው ነገር ደግሞ ራሳችንን ከዓለም ርኩሰት በመጠበቅ በቅድስና የመመላለስ ልምድ ማዳበራችን መሆኑን ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በእግዚአብሄር አብ ፊት ንጹህና ነውር የሌለበት ሃይማኖት ይህ ነው ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው መርዳትና ከዓለም ርኩሰት ራስን መጠበቅ ነው፡፡›› ያዕ 1፡27

1. ያዕ 1፡13-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ ከቁ1 ጀምሮ ስለፈተና የተናገረው በተለይም ቁ12 ላይ ፈተና የሚለው ሃሳብ እግዚአብሄር የሚስማማበትና የሚሰራበት ሆኖ የቀረበ ሲሆን፤ በቁ13-15 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ ፈተና ከእግዚአብሄር ጋራ ምንም ግንኙነት እንደሌለው ይናገራል፡፡ እነዚህ ሁለት ሃሳቦች እርስ በእርስ ይቃረናሉ ወይ? ካልሆነ ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ፡፡
2. ዘፍ 22፡1 ላይ ‹‹እግዚአብሄር አብርሃምን ፈተነው›› ይላል፡፡ ከላይ ሁለት ዓይነት ፈተናዎችን ተመልክተናል፤ የአብርሃም መፈተን ከነዚህ ከሁለቱ በየትኛው ውስጥ ትመድበዋለህ? ለምን? እግዚአብሄር የማያመጣው ዓይነቱን ፈተና ያዕቆብ ምንጩ ከየት እንደሆነ ነው በቁ13-15 ላይ የሚነግረን?
3. ሰዎች እግዚአብሄርን የክፉ ፈተና ምንጭ እንዳልሆነ እንዲረዱ ዳደረገ በኋላ፤ በቁ16-18 ላይ ያዕቆብ በአንጻሩ ሰዎች ስለ እግዚአብሄር በማያወላዳ መንገድ እንዲያውቁት የሚናገረው ነገር ምንድነው? በቁ16 ላይ ‹‹የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ አትታለሉ›› ለምን ይመስልሃል መታለል የሚለው ሃሳብ የተጨመረው? በህይወትህ ያሉት መልካም ነገሮችና በረከቶች ሁሉ ምንጩ እግዚአብሄር እንደሆነ ምን ያህል ይታይሃል?
4. ያዕቆብ በቁ17 ላይ ስለ እግዚአብሄር አለመለዋወጥ ለአንባቢዎቹ ማረጋገጥ ያስፈለገው ምክንያት ለምንድነው? የእግዚአብሄርን በጎ ስጦታና ፍጹም የሆነውን በረከት ማረጋገጫ አድርጎ በቁ16-18 ውስጥ የሚጠቅሰው አንድ ነገር ምንድነው?
5. ቁ19-21 ድን ስንመለከት ጸሐፊው አንባቢዎቹ እንዲያስተውሉት የሚፈልገው አንድ እውነት ምን ነበረ? ጸሐፊው ለሰጣቸው ምክርና መመሪያ በምክንያትነት ያቀረበውስ ነገር ምንድነው? ለመናገር አለመቸኮልና ረጋ ብሎ የመስማት ነገር በራስህ ታያለህ ወይ? ቁጣስ ይቀድምሃል ወይስ ትቀድመዋለህ?
6. ቁ22-25 ቃሉን ሰሚ ብቻ መሆን ለምንድነው ራስን ማታለል አድርጎ ያዕቆብ የሚያየው? በሥራው የተባረከ እንደሚሆን በዚህ ክፍል ውስጥ የተነገረለት ሰው ባህርይ ሆነው የተጠቀሱት ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
7. ከ18-25 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል በህይወታችን እንደሰራ ወይም ደግሞ እንደሚሰራ ሆኖ የተነገሩን ምን ምን ሃሳቦችን ትመለከታለህ?
8. ቁ26-27 ላይ ስናነብ ንጹህና ነውር የሌለበት ሃይማኖትከ የሚያተኩርባቸው ሆነው የተነገሩት ሁለት ዋና ዋና ዘርፎች ምንና ምንድናቸው? እምነትህ በሁለቱም አቅጣጫ የሚያድግ ነው ወይ? እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኝና በእርሱ ፊት ተቀባይነት ያለው አምልኮ ለመለማመድ ካስፈለገ ለሌሎች በመትረፍና በተጨማሪም ደግሞ ራስን ከዓለም ርኩሰት በመጠበቅ በቅድስና መመላለስን መለማመድ ያስፈልጋል፡፡

# <u>ጥናት ሶስት ያዕ 2፡1፡13</u>

የጥናት ዓላማ፡- በንግግራችንም ሆነ በተግባራችን አንዱን ወንድማችንን ከሌላኛው አስበልን ወይም አሳንሰን ማየት እንደማይገባንና፤ ይህንን ማድረግ ደግሞ በክርስቶስ ፊት ስንቀርብ የሚያስፈርድብን ነገር እንደሆነ እንድንረዳ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስትናገሩም ሆነ ስታደርጉ ነጻነት በሚሰጠው ህግ እንደሚፈረድባቸው ሰዎች ሁኑ፤ ምክንያቱም ምህረት ያላደረገ ሁሉ ያለምህረት ይፈረድበታል፤ ምህረት በፍርድ ላይ ያይላል፡፡›› ያዕ 2፡12-13

1. ያዕ 2፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-4 ላይ ስናነብ ያዕቆብ የሚያስተላልፈው ትዕዛዝ ምንድነው? ይህንን ትዕዛዝ እንዲሰሙና እንዲታዘዙ በአዕምሮው ውስጥ ያሉት ሰዎች እነማን ናቸው ብለህ ታምናለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
2. ‹‹…በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ እንደመሆናችሁ አድልዎ አታድርጉ፡፡›› የሚለውን አነጋገር በሮሜ 2፡11 ኤፌ 6፡9 ቆላ 3፡25 ካሉት ጥቅሶች ጋራ አብረን ስናየው አድልዎ ማድረግ ስለማይኖርብን ምክንያት ምን መማር እንችላለን?
3. በሰዎች መካከል አድልዎ ስናደርግና አንዱን ከሌላው አበላልጠን የምናይ ከሆነ ያዕቆብ በቁ4 ላይ የሚሰጠን ስም ምን የሚል ነው? ማቴ 22፡16 ከዚህ ትምህርት አንጻር የኢየሱስን ህይወት የተመለከቱት ጠላቶቹ ሲሰጡ የምንመለከተው ምስክርነት ምን ይመስላል? በሰው ዓይን ዝቅተኛ ሆነው የሚታዩትንና የከበሩ የሚመስሉትን ስለምታስተናግድበት ሁኔታ ሰዎች ስላንተ ምን ይናገራሉ?
4. በቁ1-4 ላይ ያነበብነው ሃሳብ፤ ሰው ድሃም ሆነ ሃብታም አንዱን ከሌላው አብልጠን ማየት እንደማይገባን ተነግሮን በዚህ በቁ5-7 ላይ ስናይ ደግሞ እግዚአብሄር ድሆችን እንጂ ባለጠጎችን እንዳልመረጠ መናገሩ ከላይኛው ሃሳብ ጋራ የሚቃረን ነው ወይስ ምን ሃሳብ አለህ?
5. ቁ5-7 ላይ ያዕቆብ ማንን ከማን ጋራ እያወዳደረ ነው ሲያስተምራቸው የምንመለከተው? በአንድ ቃል ብንጠቀልለው እግዚአብሄር ድሆችን ምን አደረገ ነው የሚለን? ስለ ክርስትያኖቹ ሲናገር እኛ ምን እንዳደረግን ነው የሚናገረው? በዚህ ዘመን ና ከእግሬ ሥር ተቀመጥ ባይባልም በዘመኑ ሲከሰቱ የምታዩአቸውን ነገሮች ተወያዩባቸው፡፡
6. አድልዎ ሳናደርግ ሰዎችን ሁሉ በእኩልነት ማየትና ማስተናገዳችንን የትኛውን የእግዚአብሄር ህግ እንደጠበቅን አድርጎ ነው ያዕቆብ የሚናገረው? ሰውን በእኩልነት አለማየት ወይም አድልዎ መፈጸም የሚለውን ሃሳብ ያዕቆብ በቁ9 ላይ በቀጥታ ምን ብሎ ነው የሚጠራው?
7. በቁ12-13 ላይ ጸሐፊው ጌታ ሲመጣ ሊያስፈርዱብን ስለሚችሉ ሁለት ነገሮች ይናገራል፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በሮሜ 8፡1 ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑት ከእንግዲህ ኩነኔ እንደሌለባቸው ይነግረናል፤ ታዲያ ከፍርድ ካመለጥን ያዕቆብ እንድንጠነቀቅ የሚነግረን ስለየትኛው ፍርድ ነው?
8. በሰዎች መሃል አድልዎ ማድረግ ሃጥያት ለፍርድ የሚያበቃ ድርጊት ከሆነ ያዕቆብ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እንዴት እንድንኖር ነው የሚመክረን? በሰው ላይ አድልዎ እንዳደረግህ የምታስታውሰው ነገር ካለህ በጌታ ፊት ንስሃ ግባበት፡፡

# <u>ጥናት አራት ያዕ 2፡14-26</u>

የጥናት ዓላማ፡- የሰዎችን አለባበስ አይቶ አለመናቅ፣ አለማዳላትና እንደ ማንኛውም ሰው ማየት ብቻ በቂ ሳይሆን፤ ይህ ወንድም ወይም ይህች እህት የሚገኙበትን የችግር ሁኔታ የማቃለል ችሎታው በእጃችን እስካለ ድረስ የሚያስፈልጋቸውን የማድረግም ግዴታ ጭምር እንዳለብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አንድ ወንድም ወይም አንዲት እህት የሚለብሱት ልብስም ሆነ የሚመገቡት ምግብ አጥተው፣ ከእናንተ መሃል አንዱ በሰላም ሂዱ፤ አይብረዳችሁ ጥገቡ ቢላቸው፣ ለሰውነታቸው ገን የሚያስፈልጋቸውን ባይሰጣቸው ምን ይጠቅማቸዋል?›› ያዕ 2፡15-16

1. ያዕ 2፡14-26 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ14 ላይ ከያዕቆብ አነጋገር ሊያድን የሚችል ትክክለኛ እምነት ምን ዓይነት ነው? ከቁ14 በመነሳት የራሳችንን ህይወት ለመመዘን ስንፈልግ ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ ምንድነው?
2. ቁ15-17 ላይ የተጠቀሱትን ወንድምና እህት በማየት ስለ ድህነት ወይም ችግር ልንረዳ የምንችላቸውንና ለአንተ የሚታዩህን እውነቶች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ‹‹…ምን ይጠቅማቸዋል?›› የሚለው በቁ16 ላይ የሚገኘው አነጋገር እምነታችን ከራሳችን አልፎ በሌላው ሰው ህይወት ውስጥ ሊያስገኝ ስለሚያስችለው ነገር ምን እንማራለን?
3. ቁ18-19 አንድ ሰው እምነት ኖሮት ሥራ ላይኖረው ይችላል ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ እኛ ክርስትያኖች ባለን እምነትና ያዕቆብ አጋንንትም እምነት እንዳላቸው በተናገረው መሃል ያለን ልዩነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. ያዕቆብ በቁ20 ላይ ‹‹አንተ ከንቱ ሰው›› በማለት የሚነቅፈው ማንን ይመስልሃል? በዚህ ክፍል ውስጥ ጸሐፊው የእምነትን ዋጋ ቢስነት ለማረጋገጥ ነው ወይ እየሞከረ ያለው? ካልሆነስ የያዕቆብ ይህንን ሁሉ የሚናገርበት ዓላማው ምንድነው?
5. ያዕቆብ ሰዎች እምነታቸውን በሥራ መደገፍ ይኖርባቸዋል ብሎ ያቀረባቸው ሁለቱ የብሉይ ኪዳን ሰዎች ማንና ማን ናቸው? እነዚህን በህይወታቸው እጅግ የተራራቀ አኗኗርን የኖሩ ሁለት ሰዎች መርጦ ያቀረበበት ምክንያት ለምንደነው ብለህ ታምናለህ?
6. ‹‹አብርሃም በእግዚአብሄር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት›› የሚለውን በዘፍ 15፡6 ላይ የሚገኘውን ጥቅስ ጳውሎስ በሮሜ 4፡3 እና ያዕቆብ ደግሞ በ2፡23 ላይ የተለያየ እውነትን ለማስተማር በማስረጃነት ሲጠቅሱት እናያለን፡፡ በነዚህ ሁለት ጸሐፊዎች የሚታየውን ቅራኔ የሚመስለውን ሃሳብ እንዴት እንደምታየው ለወገኖች ተናገር፡፡፡
7. ያዕቆብ በምዕ 2፡1-13 ላይ በማድረግ የሚመጣን ሐጥያት ሲያሳየን፤ በቁ14-26 ላይ ደግሞ ባለማድረግ የሚመጣን ሃጥያት ያሳየናል፡፡ በማድረግ የሚመጣው ሐጥያት ምንድነው? ባለማድረግ የሚመጣውስ? አንተን የሚያስቸግርህ በድሆች ላይ አድልዎ ማድረግ ነው ወይስ ለተቸገሩና ለሚያስፈልጋቸው አለመድረስ? በሰዎች መሃል አድልዎ አለማድረጋችንን ብቻ ሳይሆን ማየት የሚኖርብን፤ ለድሆች ወገኖቻችን የሚያስፈልጋቸውን ማድረግም ከእውነተኛ አማኝ ስለሚጠበቅ፤ አንዱን ይዞ ሌላውን መጣል የሚባል ነገር የለም፡፡

# <u>ጥናት አምስት ያዕ 3፡1-18</u>

*የጥናት ዓላማ፡- የማያምኑ ሰዎች አንደበታቸውን መግታት ቢቸገሩም እንኳን፤ እኛ አማኞች ግን አንደበታችን አምላክን እና ሰዎችን የምንባርክበት እንጂ በምንም ዓይነት ለእርግማን መጠቀም እንደማይገባን ለመማር፡፡*
*የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በምላሳችን ጌታንና አብን እንባርካለን፤ በእርስዋም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን፤፡፡ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ ይህ ሊሆን አይገባም፡፡›› ያዕ* 3፡9-10

1. *ያዕ* 3፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2ትን ስናነብ ለአንባቢዎቹ የጸሐፊው ምክር ምንድነው? ለዚህ ምክር እንደምክንያት አድርጎ የሚናገረውስ ነገር ምንድነው? ስለ ጸሐፊው ከምናውቀው ነገር አንድ ተጨማሪ ነገር እንደናውቅ የሚያደርገንና ስለራሱ የሚነግረን አንድ እውነት ምንድነው?
2. ያዕቆብ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ያሉትን አስተማሪዎች ተስፋ ለማስቆረጥ ነው ወይ ይህንን አይነት አነጋገር የሚናገረው?
3. በቁ3-6 ላይ ጸሐፊው ሃሳቡን ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህን ነገሮች በማስታከክ ያዕቆብ ለአንባቢዎቹ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና ሃሳብ ምንድነው?
4. በቁ7-8 ባለው ክፍል ውስጥ ያዕቆብ የምላስን ሁኔታ ለመግለጥ ለማነጻጸር የተጠቀመባቸው ምን ነገሮችን ትመለከታለህ? ያዕቆብ እነዚህን ሁሉ ነገሮች በማነጻጸርያነት ተጠቅሞ በመጨረሻ ስለ ምላስ የደረሰበት ድምዳሜ ምን የሚል ነው?
5. ያዕቆብ በተፈጥሮ ዓለም ውስጥ ሊሆኑ አይችሉም ብሎ በቁ9-12 የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህን በተፈጥሮ ሊሆኑ የማይችሉ እንግዳ የሆኑ ነገሮች ያዕቆብ መናገር ያስፈለገው ዋነኛው ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
6. በቁ10 ላይ ያዕቆብ ክርስትያኖቹን የሚያዘው ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ምን የሚል ነው? በቁ7-9 ላይ ምላስን መቆጣጠር እንደማይቻል አድርጎ ሲናገር፤ በዚህ በቁ10 ላይ ደግሞ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ማውጣት እንደሌለባቸው ማለትም ምላሳቸውን እንዲቆጣጠሩ ሲያዛቸው ይታያል፡፡ ምላስም መቆጣጠር አይቻልም ካለ ለምን ተቆጣጠሩ ብሎ ሊናገራቸው እንደሚችል አስረዳ፡፡
7. በቁ13-18 ውስጥ ስንት የጥበብ ዓይነቶችን እንደምታይና እነዚህም የጥበብ ዓይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ እነዚህ ሁለት የጥበብ ዓይነቶች በሰዎች ህይወት ውስጥ በምን ሁኔታ ሊገለጡ እንደሚችሉ ነው ክፍሉ የሚያስተምረን? በዚህ ክፍል ውስጥ ያዕቆብ ለምድራዊው ጥበብ ምንጭ አድርጎ የተናገራቸው ሌሎች ነገሮች ምንድናቸው?
8. በቁ13 ላይ ‹‹ከእናንተ መካከል ጥበበኛና አስተዋይ የሆነ ሰው… ሥራውን ከጥበብ በሆነ በመልካም አኗኗር ያሳይ›› ይላል፡፡ ከዚህ አነጋገሩ ጋራ ከታች በቁ14-18 ያሉት ሃሳቦችን የተናገረው ለምንደነው ብለህ ታምናለህ?
9. በቁ13 መልካም አኗኗርን ሲያጎላ፤ ቁ10 ደግሞ መልካም አነጋገር ላይ ያተኩራል ያጎላል፡፡ ‹‹ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ ይህ ሊሆን አይገባም፡፡›› ይህ ምክር በማን ላይ ያተኮረ ነው ብለህ ታምናለህ? በአንደበትህ ጌታን የምትባርከውን ያህል እርግማንም ይቀልሃል ወይ? አንደበትህን እግዚአብሄር አምላክን ለመባረኪያ እንጂ ወንድም እህትን ለመርገሚያ ስላልሆነ ምላስህን ለበረከት ተጠቀምበት፡፡

# ጥናት ስድስት ያዕ 4፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- እኛ አማኞች ማድረግ የሌለብንን ማድረጋችን ሃጥያት እንደሆነ የተቀበልነውን ያህል፤ ማድረግ የሚገባንን መልካም ነገር ከቃሉ ተምረን ያወቅነውንና የተረዳነውን አለማድረጋችንም ሃጥያት እንደሆነ ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንግዲህ መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለበት እያወቀ የማያደርግ ሰው ሃጥያት ያደርጋል፡፡›› ያዕ 4፡17

1. ያዕ 4፡1-17 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ላይ በቅዱሳኑ ጉባኤ መሃል መታየት የሌለበት ነገር ግን እየታየ ያለው ነገር ምንድነው? ያዕቆብ ለዚህ ክፉ ነገር ምንጭ ነው በማለት የሚናገረው ነገር ምንድነው?
2. እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን ለማግኘት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምን ምንድናቸው? እነዚህን ሁሉ እያደረጉ የማያደርጉት፤ ነገር ግን ይህንን ቢያደርጉ የሚፈልጉትን ነገር ማግኘት የሚችሉበት መሳሪያ ምንድነው ብሎ ነው ያዕቆብ የሚናገረው? እግዚአብሄርን ለምነው እንኳን መቀበል የማይችሉበት ምክንያት ለምንድነው? ያንተስ ጸሎት በራስህ ስጋዊ ምኞት ዙሪያ ነው ወይስ የጸሎትህ ትኩረት ምን ይመስላል?
3. በቁ4 ላይ ሲናገር ‹‹አመንዝሮች ሆይ፤ ከዓለም ጋራ ወዳጅ መሆን የእግዚአብሄር ጠላት መሆን እንደሆነ አታውቁምን? ይላል፡፡ ያዕቆብ ለምን ይመስልሃል የዚህ ዓይነቱን ሃይለኛና ከባድ የሆነ አነጋገር የተጠቀመበት ምክንያት? በዚህ ቁጥር አነጋገር ሰው ጓደኛን አስመልክቶ ያሉት ሁለት አማራጮች ምንና ምንድናቸው?
4. በቁ4-6 ላይ ስንመለከት ስለ እግዚአብሄር ባህርይ መረዳት የምንችለውና እርሱም በቃሉ የሚያረጋግጥልን አንድ እውነት ምንድነው? በአንተ አመለካከት ለምን ይመስልሃል ለዓለምና ለእግዚአብሄር አንድ ሰው ለሁለቱም በአንድ ጊዜ ጓደኛ መሆን የማይቻለው?
5. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ፤ የዓለምን ወዳጅነት በመጣል የእግዚአብሄር ወዳጅ ለመሆን ከልቡ ለሚፈልገው የእግዚአብሄር ህዝብ የተገባለት ምን ቃል ኪዳን ትመለከታለህ?
6. ቁ7-10ን ስንመለከት ‹‹እግዚአብሄር ትዕቢተኞችን ይቃወማል…›› ብሎ ከተናገረው ጋራ በቁ7 ላይ ስለ ዲያቢሎስ መቃወም ከሚናገረው ሃሳብ ጋራ ምን ግንኙነት ሊኖረው እንደሚችል አስረዳ፡፡ ይህ ቁጥር ዲያቢሎስን ከመቃወማችን በፊት በቅድሚያ ልናደርገው ስለሚገባን ነገር ያዕቆብ ምን ይነግረናል? ወደ እግዚአብሄር መቅረባችንን የሚያመለክቱ በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ የሰፈሩትን ነገሮች ዘርዝር፡፡
7. ቁ11-12 ለአንባቢዎቹ እየሰጠ ያለው ማስጠንቀቂያ ምንድነው? ይህንን ማድረግ የለለባቸው ለምንድነው ይላል? በወንድምህ ላይ ስትፈርድ የእግዚአብሄርን ሥፍራ እየወሰድክ እንደሆነ ይገባሃል ወይ?
8. 13-16 ያሉት ቁጥሮች የሚያተኩሩት በምን ዓይነት ሰዎች ላይ ነው? ያዕቆብ የእነዚህን ሰዎች ድርጊት ትክክል እንዳልሆነ ሲናገር፤ ሰዎች በተለይም ክርስትያኖች ለህይወታቸው እቅድ እንዳያወጡና በዘፈቀደ እንዲኖሩ ማበረታታቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡ ከነዚህ ቁጥሮች በአጠቃላይ ስለህይወታችን ምንነት መማር የምንችለው ነገር ምንድነው?
9. ቁ17ትን ስናነብ ሃጥያት ሆኖ የተነገረን ነገር ምንድነው? መልካም እንደሆኑ የምታውቃቸው፤ ነገር ግን የማታደርጋቸው ነገሮች ወደ አዕምሮህ የሚመጡልህ ካሉ ለወገኖች አካፍል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ክርስትና ማድረግ የሌለብንን ስናደርግ ሃጥያት እንደሆነ እንጂ ማድረግ የሚገባንን አለማድረጋችን ሃጥያትነቱን እንደሚገባ ትኩረት ባይሰጠውም እንኳን መልካም የሆነውን እያወቁ አለማድረግም ሃጥያት መሆኑን ልትገነዘብ ያስፈልግሃል፡፡

# ጥናት ሰባት ያዕ 5፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- በጸሎታችን እግዚአብሄር ታላቅ ነገርን እንዲሰራ፤የሚያስፈልገው የእኛ የተለየን ዓይነት ሰዎች መሆን ሳይሆን፤ ጸሎታችን እንደ ኤልያስ ከልብ የመነጨና በእምነት የሚጸለይ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት ሃይል አለው፤ ታላቅ ነገርም ያደርጋል፡፡ ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ፤ ዝናብ እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድር ላይ ሶስት ዓመት ተኩል ዝናብ አልዘነበም፡፡›› ያዕ 5፡16-17

1. ያዕ 5፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ ያዕቆብ ምዕራፍ አምስትን ሲጀምር ለሃብታሞች የሚናገረው ነገር ምንድነው? ጸሐፊው አርቆ ሲያይ እነዚህ ሰዎች አከማችተዋቸው ሰለነበሩት ነገሮች ምንን ነው የሚያየው? እንዴት ነው ዝገቱ በነዚህ ሰዎች ላይ ሊመሰክርና ሥጋቸውንም እንደ እሳት ሊበላ የሚችለው?
2. እነዚህ ሃብታሞች ሃብታቸውን ያከማቹት በምን ዓይነት መንገድ ነው? እነዚህ ሰዎች የበዘበዟቸውና ደመወዛቸውን የከለከሏቸው ሰዎች ማድረግ የሚችሉትና እያደረጉ ያሉት አንድ ነገር ምንድነው? ይህንን ክፍልና ሌሎችንም ተመሳሳይ ሃሳቦች ስንመለከት፤ እግዚአብሄር ከማን ጋራ ሲቆም ነው የምናየው?
3. በቁ7-9 ላይ ለአንባቢዎቹ ምን በማለት ነው የሚመክራቸው? ከገበሬ ትዕግሥት ጋራ ትዕግሥታቸውን እያነጻጸረ የሚናገራቸው ምን በማለት ነው? በነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ የጌታን ምጽዓት ነገር የሚናገሩ ቢያንስ ሃሳቦችን ማየት እንችላለን፡፡ እነዚህን የት እንደሚገኙ ለወገኖች ጠቁም፡፡
4. ቁ10-11ድን ስናነብ፤ የጌታን ነብያት የምን ምሳሌዎች አድርገን እንድንመለከታቸው ነው ጸሐፊው የሚመክረን? በሁኔታዎች ውስጥ በትዕግሥት የጸኑትንና ያለፉትን ሰዎች ያዕቆብ እንዴት ተደርገው እንደሚቆጠሩ ነው የሚያሳስበን? በዚህ ክፍል ጸሐፊው የኢዮብን ትዕግሥት ምሳሌነት ከመናገር ጋራ በማያያዝ ሊያስተምረን የፈለገው እውነት ምንድነው ትላለህ?
5. ቁ12 ላይ ወንድሞች በማለት ያዕቆብ ለሚጠራቸው ሰዎች ምክሩ ምንድነው?
6. ቁ13-15 ሲጀምር ‹‹በእናንተ መካከል›› ሲል እነማንን ሲጠቁም ነው? በዚህ መሃል ሊኖሩ የሚችሉ የሚዘረዝራቸው ስንት ዓይነት ሰዎችን ታያለህ? እነማን እንደሆኑ ዝርዝራቸውን ተናገር፡፡ በቅዱሳን መሃል ሁሉም ሰው በመከራ ውስጥ እንዳልሆነ፣ ሁሉም ሰው ደስተኛ እንዳልሆነ፣ ወይም ደግሞ ሁሉም ሰው በሽተኛ እንዳልሆነ መረዳት ለምን ይጠቅማል ታላለህ?
7. በቁ14 ላይ ‹‹ከእናንተ መካከል የታመመ ሰው አለ? የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎችን ይጥራ፤ እነሱም በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፡፡›› ይላል፡፡ ይህ ማለት የታመመ ሰው ሁሉ የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች መጥተው ካልጸለዩለት በስተቀረ አይፈወስም ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ እንደሆነ ነው የምትረዳው? ይህ ክፍል ከሰዎቹ ማንነት ይልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነገር ምን ሆኖ ነው የምናየው?
8. ቁ17 ላይ የኤሊያስን ምሳሌ ማምጣት ያስፈለገው ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ስለኤሊያስ ማንነትና ስለ ጸሎቱ ዓይነት ከዚህ ምንባብ ውስጥ ማየት የምንችላቸውን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ጠቅሰህ ተናገር፡፡
9. በቁ14-18 በሚገኘው ክፍል ላይ ሐዋርያው ያዕቆብ ጸሎትን አስመልክቶ ሊያስተምረን የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው? ራስህን ለጸሎት የማይበቃ ሰው አድርገህ ታያለህ ወይ? ስትጸልይስ እንደ ኤልያስ ከልብህ ትጸልያለህ ወይስ የግብር ይውጣ ጸሎት ነው የምታቀርበው?